# ክቡር የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንኳን ደኅና መጣህ

ክቡር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ፤

ክቡር አቶ ለማ መገርሳ ፤

ሹምና ሽማግሌ ማን እንደሚባባሉ የሆነ ታሪክ በማንሣት ልጀምርና ፥ አለቃ ምላቴ የሚባሉ ሽማግሌ ንጉሥ ምኒልክን ሊያስታርቁ ወደ አፄ ዮሐንስ ሄደው ነበር ። አለቃ ምላቴ አፄ ዮሐንስ ዘንድ ሲደርሱ ፥ ንጉሡን ወጣት ጎልማሳ ሆነው አገኟቸው ። ሽማግሌው ጉዳያቸውን ከማቅረባቸው በፊት ፥ አፄ ዮሐንስን ፥ "እርስዎ እንዳልል ሕፃን ነህ ፤ አንተ እንዳልል ንጉሥ ነህ ምን ይሻላል?" ቢሏቸው አፄ ዮሐንስ ፥ "ፈቅጀልዎታለሁ አንተ ይበሉኝ" አሏቸው ።

ክቡር ዶክተር ዐቢይ ፤ ክቡር አቶ ለማ ፤ በልባችሁ ያለውን ትሕትና ሰሞኑን ሳነብ ፥ "አንተ" እያልኩ ሳማችሁ እንደነበረው እንድቀጥል እንደፈቀዳችሁልኝ አይቻለሁና ፥ በአሜሪካ በድዮስጶራ ደረጃ ያለነውን ኢትዮጵያውያን ስላልረሳችሁን እያመሰገንኩ ፥ እንኳን ደኅና መጣችሁ እላለሁ ። "እነሱ በሰላም ይኖራሉ" ብላችሁ ሳታስቡ እኛን ፍለጋ ስለመጣችሁ ፥ መጠን-አልባ ደስታየን እገልጽላፍኋለሁ ። እርግጥ ነው ፥ ባለንበት አገር ከፖሊስ ጋር እስካልተፋጠጥን ድረስ በሰላም እየወጣንና በሰላም እየገባን በሰላም እንኖራለን ። ግን ሰላም ማለት በሰላም ወጥቶ ከመግባት ያልፋል ። ከወገናችን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያለን ግንኙነት የመንፈስ ብቻ ሳይሆን የአካልም ስለሆነ ፥ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ላይ የሚደርሰው ደስታ ያስደስተናል ፤ የጨቋኝ ገዢ ጥቃት እናንተን ያምማችሁ እንደነበረ እኛንም ያመን ነበረ ።

ልዑል እግዚአብሔር እናንተን ስለሰጠን ፥ በምናመሰግንበትና በምንደሰትበት ጊዜ ፥ የረዳቶቻችሁን የኢንጅኔር ስመኘው በቀለን መገደልና የአቶ ተስፋየ መኰንን ዜና ዕረፍት ሰማን ። ነፍሳቸውን ከሰላሙ ቦታ ያሳርፍልን ። ለናንተና ለቤተሰቦቻቸው ጽናቱን ይስጣችሁ ። ክቡር ዶክተር ዐቢይ ፤ ደቡብ ኮርያን ከኋላ ቀርነት ያወጣትን የፕሬዚዴንት የሜጀር ጄኔራል ፓርክን ቹንግ ሂንታሪክ የተረክልን አለምክንያት አይደለም ።

ምዕራባውያን ከማህላቸው አንድ ስም ያወጣ ሰው (celebrity) ሲያዩ ፥ ሊነኩትና ሊጨብጡት ሲጋፉ ሳይ ፥ በመገረም እታዘባቸው ነበረ ። አሁን ገባኝ ፤ የታሪክ ሰዎቼን በአካል በማየቴ ዕድለኛ ነኝ ። አምላኬ ስለ ሀገራችን ላየውና ልሰማው የምመኘው ታሪክ እስከሚፈጸም እስከ ዛሬ ድረስ ስላቆየኝ ፥ እንደ ሽማግሌው ስምዖን ፥ "እስመ ርእያ አዕይንትየ አድኅኖትከ" (ዐይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና) እለዋለሁ ።

ክቡር ዶክተር ዐቢይ ፤ ባጭር ጊዜ ውስጥ የፈጸምካቸውን ሥራዎች ያዩ ፥ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተርነት የተሾምክበትን መጋቢት 24 ቀንን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ ከገቡበት ከሚያዝያ 27 ቀን ጋር ያመሳስሉታል ። "ያለፈውን በይቅርታ እንለፈው" አልከን እንጂ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት 50 ዓመታት የደረሰበት ሥቃይ በ5ቱ ዓመት የፋሺስት ወረራ ዘመን ከደረሰበት

ሥቃይ በዓይነትም በብዛትም የላቀ ነው ። የየካቲት 12ን ጭፍጨፋ ትተን ፥ በፋሺስት ዘመን የኢትዮጵያውያን ዓሥር ጥፍሮች አንድ ባንድ አልተነቀሉም ። እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ቁልቁሊት ተሰቅለው አልተገረፉም ። ጣልያኖች በወንድ ብልት ላይ ውሀ የሞላበት ጠርሙስ አላንጠለጠሉበትም ። አካለ ጎደሎ የሚያደርግ ቅጣት አልቀጡም ። ከፋሺስቶቹ ጋር የሚመሳሰሉት ለኢትዮጵያ የምናለቅሰውን ኢትዮጵያውያንን ሁለተኛ ዜጎች በማድረግ ብቻ ነው ። ማናቸውም መንግሥታዊ አገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጠው ለጎሳቸው ሰዎች ነበር ።

ጣልያኖች ኢትዮጵያን በመያዛቸው ፥ "ንጉሣችን የአንድ ጥንታዊትና ታላቅ አገር ንጉሠ ነገሥት ሆነ" ብለው ኵራት ተሰምቷቸው ነበር ። የዘመኑ ገዢዎቻችን ግን ልጆቻችንን ታሪክ-አልባ አድርገው አሳደጉብን ። አንተ ራስህ የጨቋኞችን ወንጀል ስትገልጽ ፥ "ብዙዎች በየቀኑ ከቤታቸው መውጣታቸውን እንጂ ፥ ወደ ቤታቸው መመለሳቸውን እርግጠኛ መሆን ተስኗቸዋል" ብለህ በአንድ አረፍተ ነገር አጠቃለኸዋል ።

መጋቢት 24 ቀን ኢትዮጵያውያን ከታሰሩባቸው ሁለት እግር ብረቶች አንዱ ፥ ጭቆና የተባለው እግር ብረት ፥ የተፈቱበት ቀን ነው ። ስለዚህም ሳንፈራ እንጽፋለን ፥ ሳንሰጋ እንናገራለን ፥ ሳንገላመጥ እንሰበሰባለን ። ከፍርሃት ነፃ ወጥተናል ። ሁለተኛው እግር ብረት ሲፈታልን ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ መጋቢት 24 ቀንን በየዓመቱ የለማ መገርሳንና የዐቢይ አሕመድን ስም እየጠራ ሲያከብረው ይኖራል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም አመራር ፥ ዛሬ ኢትዮጵያና ኢጣልያ ወዳጆች እንደሆኑ ሁሉ ፥ በአንተም አመራር ሁላችንም በይቅርታና በፍቅር በሰላም ልንኖር ነው ። ኢትዮጵያን ከጭቆና ነፃ ስላወጣሃትና በቀል የእግዚአብሔር መሆኑን ስላስታወስከን ከተቀመጥኩበት ተነሥቼ እጅ እነሣሃለሁ ።

በድዮስጶራ ያለነው ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሰላም ያገኘነውና "እፎይ" ብለን ያደርነው ፥ ልዑል እግዚአብሔር የሕዝቡን ሥቃይ አይቶ ፥ "ሕዝቤን ልጆቿን ከምትበላ ድመት እንድታድን ጠርቼሃለሁ" ብሎ ዐቢይን የላከው ዕለት ነው ። ያን ሌሊት እንቅልፍ ያልወሰደው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ካለ ፥ ታሪኩ ወደቅዠት እንዳይለወጥበት በመፍራት ያልተኛ መሆን አለበት ። በሽተኛ ድመት ፥ ሚዳው ሁሉ አይጥ በአይጥ ሆኖላት ሳለ ፥ የምትበላው የራሷን ልጆች ነው ። አርባ ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያ በገዛ ልጆቿ ከተበላች በኋላ ፥ አንተና ፊር ቃዳኝ አቶ ለማ መገርሳ ቁጭታችሁን ይዛችሁ ብቅ ስትሉ ፥ "በውኑ ከኢሕአዴግ ደግ ሰው ሊወጣ ይችላልን?" ያልን ጥቂቶች አልነበርንም ። አትፈርዱብንም ። ሳናስበው ፥ የተፈጥሮ ጓደኛቸውን ሳጥናኤልን ሊመቱ የተላኩትን ሚካኤልንና ገብርኤልን መሰላችሁን ።

ቅዱስ አምላካችን የሂትለርንና የስታሊንን ጀግንነት የሚኰንን ፥ የማሀትማ ጋንዲንና የኔልሰን ማንዴላን ጀብዱነት የሚያደንቅ መሪ ስላስነሣልን እናመሰግነዋለን ። አንተንም ፥ "ፈላስፋው መሪያችን ዐቢይ አሕመድ" ብየ ልጠራህ አስቤ ነበር ፤ ግን ሕዝባችን እኔ የማውቀውን ፍልስፍናህን ሲያውቅ ራሱ ይጀምረዋል ብየ ተውኩት ። ለማስረጃ ከፍተኛውን ሥልጣን ከመያዝህ በፊት ያመንክበትን ልጥቀስ ፤

መሪ የምንሆነው የግል ፍላጎታችንን ለማግኘት አይደለም ። መሪ ስንሆን ትልቅ ኃላፊነትን እንቀበላለን ። ይህም ኃላፊነት አገሪቱ ላይ ስላሉ ኅብረተሰቦች ፣ ስለሀገሪቱ ዳር ድምበር መከበር ፣ ማኅበራዊና ፖሊቲካዊ ችግሮችን ስለመቅረፍ ፣ የአገሪቱን መልካም ስም ስለመገንባት ፣ ለመጪው ትውልድ የሚሆን መልካም ሥራን ስለመሥራት ጭምር ነው ።

ድዮስጶራና ስደተኛ በመሠረቱ ይለያያሉ ። ድዮስጶራ መነሻው የዓሥራ ሁለቱ ነገደ አይሁድ ታሪክ ነው ። ድዮስጶራ ማንነቱን ይጠብቃል ። ስደተኛ ግን የተሰደደበት አገር ዜጋ ሆኖ ይቀራል ። እኛ ሁለቱንም አጣምረን ይዘናል ። የአይሁድ ድዮስጶራ የአይሁድ ነገዶችን ሁሉ እንዳቀፈ ፥ የኢትዮጵያው ድዮስጶራም የኢትዮጵያን ነገዶች ሁሉ ያቅፋል ። እንኳን ደኅና መጣህ የምንልህ ጎሳዎችና ነገዶች አንድ ሕዝብ ሆነን ነው ። ምስጋና ይድረስህና ፥ ሥልጡኗን ኢትዮጵያን ተመልሳ ከሠለጠኑት አገሮች አንዷ ስላደረግሃት ፥ ማንነቱን ይዞ ያለው ድዮስጶራ መመለስ ጀምሯል ። የማይመለሰው እያንዳንዱ ባለበት ስም አስጠሪ የኢትዮጵያ አምባሳደር ለመሆንና "በቀን አንድ ዶላር ለሀገራችሁ ስጡ" ያልከውን ለመፈጸም እንዲመቸው ነው ።

ምስጋና ይድረስህና ፥ መምጣትህን በናፍቆት የጠበቀውና ሊቀበልህ ሽሚያ የያዘው ከመረብ ወዲያና ከመረብ ወዲህ ያለ ሕዝብ ጭምር ነው ። የመረብ ወንዝ ድምበሩ የሆነበት ሕዝብ የደብረ ቢዘንን ፥ የጻዕዳ እምባ ሥላሴን ፥ የላሊበላን ፥ የደብረ ሊባኖስን ፥ የጣና ሐይቅን ፥ የደብረ ሐይቅን ፥ የዝቋላን ቅዱሳት ገዳማትና  በውስጣቸው ያሉትን  ቅዱሳን አበውን መሳለምና መባረክ ተነፍጎ ሲኖር እነሆ 27 ዓመት ሆነ ። ይህ ግፍ ኤርትራ የኢጣልያ የቅኝ ግዛት በነበረችበት ጊዜ እንኳን አልተፈጸመም ነበር ።

የግል ምኞቴን መናገር ቢፈቀድልኝ ፥ ምኞቴ ለኢትዮጵያውያን ዜጋ በክልሌ መሆን ቢቻል ፥ የኢትዮጵያና የኤርትራ ዜጋ መሆን ነበር ። አሁን ግን ፥ ሰፋ ያለ መፍትሔ ለማግኘት ደፋር እርምጃ በመውሰድህ ፥ ከምኞቴ የበለጠ ላገኝ ነው ። ሆኖም ፥  የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በኤምባሲ ደረጃ መሆኑ ጊዜያዊ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ ። ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን የሚመሩት ቢሮውን አዲስ አበባና አስመራ ያደረገ ጉዳይ ፈጻሚ ኮሚሽን ቢቋቋም ይበቃ ይመስለኛል ።

በሄድክበት ቦታ ሁሉ አቤቱታ እንደሚቀርብልህ ፥ እኔም አንድ አቤቱታና አንድ ስጦታ ይዤልህ ቀርቤያለሁ ። አቤቱታየ ላንተ አዲስ አይደለም ፤ በብዙ ቦታ የሰማኸው ፥ "እንዳንደመር ሕግን ተንተርሶ የከለከለንን ክልል የሚባለውን ሁለተኛውን እግር ብረት ፍታልን" የሚል ሲሆን ፥ ስጦታው የክልልን መሥመር ከኢትዮጵያ ካርታ ላይ የምትፍቅበት ላጲስ ነው ።

የአቤቱታችን ምክንያት ላንተ የተሰወረ አይደለም ። ክልል ሕዝባችንን "የሚጠረንፍ" ሰብአዊ መብትን የሚጥስ እግር ብረት ነው ። በእግር ብረት የታሰረ ሰው ወዲያ ወዲህ ማለት አይችልም ። ጎሳዎች የሰፈሩበትን በክልል መወሰንና የግላቸው ማድረግ በአንድ በኩል ሌሎች እዚያ እንዳይኖሩ እግራቸውን ማሰር ሲሆን ፥ በሌላ በኩል መብታቸውን መጣስ መሆኑን "በሰጋር በቅሎ እሰጥ" ተሟግቼ እረታለሁ ።

ለክልል ሕጋዊ ድጋፍ መስጠት ፥ “ሚችና ሕዝብ ገዳይ ነው” ያልከውን አደገኛ አስተሳሰብ እንዳይሞት ማድረግ ነው ። ሰብአዊ መብት መጣስ ደግሞ በዘመነ ዐቢይ አክትሟል ። በክልል የተከፋፈልነው የጎሳዎችንና የነገዶችን መብት ለመጠበቅ ከሆነ ፥ ጎሳዎችና ነገዶች ከፈለጉት ቦታ ሰፍረው በነፃ ከመኖር የበለጠ ፥ ከሌላ ወስዶ ለነሱ የሚሰጥ መብት የለም ።

ኢትዮጵያዊነት ጎሳዎችን እንዲጨፈልቅ ፥ ጎሳዊነት ኢትዮጵያዊነትን እንዲያደበዝዝ ማንም አይፈልግም ። ሁለቱ ሳይጋጩ ተጋምደው እስከዛሬ እንደኖሩት ወደፊትም እንዲኖሩ ማድረግ የመንግሥት ብሔራዊ ግዴታ ነው ። ብዙ ማንነትን ሳይከለሉ መያዝ የተለመደ ነው ። ለምሳሌ ፥ አንድ ሰው አባት ፥ ልጅ ፥ ወንድም ፥ አጎት መሆን ይችላል ። እንዲሁም ጎሳነትንና ኢትዮጵያዊነትን መያዝ ፥ የግልና የጋራ ቋንቋ ማወቅ ይቻላል ። ይኼ ዓይነት ሁኔታ በብዙ አገሮች የተለመደ ነው ።

ጎሳዎች እንዳይጠፉ እንፈልጋለን ። በጎሳዎች መኖር ምክንያት ነው የጥንት ቋንቋዎች መኖራቸውን ያወቅነው ። ሆኖም ፥ ጎሳዎችን በሕይወት የሚያኖራቸው ባህላቸውን ማዳበር እንጂ ፥ ሌሎችን ባለማስጠጋት አይደለም ። እናት ኢትዮጵያን በክልል መካፈል አገር መግደል ነው ። እንካፈላት ብንልም እንኳን ፥ በክፍያው እንደምንጣላ ይኸው እያየነው ነው ።

የክልል ፅንሰ ሐሳብ ኋላ ቀሮችን ለማስደሰት የተረገዘ ነው ። ማንንም ቢሆን በወንጀል ማስደሰት ወንጀል ስለሆነ ፥ ፅንሱን አስወርዱት ። ኋላ-ቀርን በወንጀል ከማስደሰት ፥ ወደሥልጣኔ ቢስቡት የበለጠ ይጠቀማል ። እየሆነ ያለው ግን የሠለጠኑትን ወደኋላ-ቀርነት መሳብና “ጎሳችን ፥ ክልላችን” እንዲሉ ማድረግ ነው ።

“ተደመሩ” ስትለን እንዳንታዘዝ ፥ የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ይከለክለናል ። በመደመር ምልክት የተደረደሩ ብዙ ቍጥሮች መደመራቸው የሚታወቀው ውጤቱ በአንድ ቍጥር (በኢትዮጵያዊነት) ሲሰጥ እንጂ እንደተደረደሩ መቅረት አይደለም ። እንደ እውነቱ ከሆነ ፥ ሕገ መንግሥታችሁ ሊያየን እንጂ ጥንትስ እግዚአብሔርና ታሪክ አስተፃምረውን ነበር ። “የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ” ብለህ ስትጠራን ፥ መልስ የሚሰጥህ የትኛው ጎሳ ብቻ ነው? ጥሪው “እኔን አይመለከትም” የሚለውስ የትኛው ጎሳ ነው?

እንደ ኢትዮጵያ በሠለጠኑት አገሮች ፥ ለጎሳዎች የሚሰጣቸው ዕውቅና ብቻ ነው ። ሕግ የሚወጣውም ሕዝቦች በፈለጉት ቦታ እንዲሰፍሩ ነፃነታቸውን ለማስከበር እንጂ ፥ የሰፈሩበትን አካባቢ የነሱ የግል ንብረት የሚያደርግ ሕግ አይደነገግም ። ግለ ሰብና ነገድ መኖሪያቸውን ለመወሰን መብታቸው እኩል ነው ። ጎሳዎች የተመሳሳይ ግለሰብ ጥርቃሞዎች እንጂ ፥ የጋራ መሬት ያላቸው ተቋማት አይደሉም ። ጎሳዎች እንደ ከተማ ነዋሪዎች ናቸው ። የአንድ ከተማ ነዋሪዎች ሌላ ሰው አይምጣብን አይሉም ። መሬቱንም በጋራ ፥ በማኅበር አልያዙትም ።

ነገዶችና ጎሳዎች የሰፈሩበትን ቦታ እንደማንም ግለሰብ መርጠው የሰፈሩበት ፥ ከፈለጉም ለቀውት የሚሄዱት እንጂ ፥ እዚያ አልበቀሉበትም ። ዘመኑ ይለያይ እንጂ ፥ ሁላችንም በመሠረታችን መጤዎች ነን ። መጤነት ይቀጥላል ፤ ማቆሚያ የሌለው ከአምላክ የተሰጠ የተፈጥሮ ሂደት ነው ። የሕገ መንግሥት ግዴታ የተፈጥሮ ሂደቱን ተቀብሎ ዜጎች መስፈሪያ ቦታቸውን የመምረጥ መብታቸውን ማስከበር እንጂ ፥ በፈጣሪና በታሪክ እጅ ጣልቃ ገብቶ ቦታ መረጣ ሊፈቀድለት አይገባም ። የትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊመጣበትና ሊሰፍርበት ፥ ጥሎትም ሊሄድ መብት ያለው የኢትዮጵያ ንብረት ነው ። አንተ ያልከውን ልድገመውና ፥ "ፈረሱና ሜዳው ብቻ ሳይሆን ጋላቢውም ጭምር አንድ የጋራ ሀብት ነው ።"

በሕዝብ ማህል ያሉ ልዩነቶች ተቈጥረው የማያልቁና ከፖለቲካ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ጉዳዮች ናቸው ። ለጎሳዎች ትኲረት የሰጣችሁት ተገድዳችሁ ሊሆን ይችላል ። ግን ለጎሳ ሕይወት ትኲረት የሚሰጡ አንስሮፖሎጅስት ብቻ ናቸው ። ፖለቲከኞች ዘንድ ግን የክልል ጉልሕ አስተዋፅኦ የኢትዮጵያን ሕዝብ መብት መንሣትና መከፋፈል ብቻ ነው ፤ ሁለተኛም ፥ የፌዴራሉ መንግሥት ሹመት በሚሰጥበት ጊዜ ፥ ሥልጣን አከፋፋዩ የሚያየው ችሎታንና ታማኝነትን መሆኑ ቀርቶ ፥ ጎሳን ሊሆን ነው ። እንዲህ ከሆን ደግሞ ፥ ሥራው ይጐዳል ፥ ሹመቱም ለጎሳዎቹ ሁሉ ስለማይዳረስ ፥ የሚያኮርፍ ሊነሣ ይችላል ። ክልልን እንዳለ ያቆያችሁት የምታፈርሱበት የማይቀረቁር ዘዴ ገና እየፈለጋችሁ ነው እንጂ ፥ ልትገረስሱት ሳትፈልጉ የቀራችሁ አይመስለኝም ።

ክቡር ዶክተር ዐቢይ ፤ የግል ምኞትም አለኝ ። እሱዉም ፥ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞ ስሙ እንዲመለስለትና "የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ" እንዲባል ነው ። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የተሠራው ንጉሠ ነገሥቱ በሰጡት በግል ርስታቸው ላይ ነው ። ከተማው ትልቅ ስለሆነ ፥ በአዲስ አበባ ስም የሚጠራ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ይቋቋምልን ።

ክቡር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ፤ አንተና ክቡር አቶ ለማ መገርሳ የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ አባቶች እንድትሆኑ እንደ ሙሴና እንደ አሮን የተጠራችሁ ናችሁ ። ግን መጨረሻችሁ እንደሙሴ እንዳይሆን እንጸልይላችኋለን ። ሙሴ የመራው ሕዝብ ከሀገረ ተስፋ ሲገባ ፥ እሱ አብሮ እንዳልገባ ጠቅሰህልናል ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ ሀገረ ዲሞክራሲ እየመራችሁ አብራችሁ እንድትገቡ እንጸልያለን ። በምታዘጋጁት ገለልተኛ ምርጫ ፓርቲዎች ሲወዳደሩ እንድታዩና ይኸን ትልቅ ታሪክ ለመሥራት የጠራችሁን አምላክ ነፃ ከአወጣችሁት ሕዝብ ጋራ ስታመሰግኑት ልናይና ልንሰማ እንመኛለን ።

ስለሆነም ፥ ከጥንቃቄ ጒድለት ምክንያት አንዳች ነገር ቢደርስባችሁ ፥ አደጋው የሚደርሰው በሁላችንም ላይ ነው ። ከማህላችን የሚተርፉ ካሉ ፥ ከሚያዝኑላችሁ የሚያዝኑባችሁ ይበልጣሉ ። የኢትዮጵያ አምላክ በሰላም ፥ በጤና ፥ በደስታ ወደ አገራችሁ ይመልሳችሁ ። አሜን ወአሜን ።

ጌታቸው ኃይሌ ። ሚኒያፖሊስ ፥ ሚኒሶታ ፥ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፥ ፳፻፲ (July 30, 2018.)